ፍኖተ ዴሞክራሲ የኢትዮጵያ አንድነት ድምጽ

Finote Democracy Voice of Ethiopian Unity

Efdpu@aol.com www.Finote.org

## ወርቁ ቢጠፋ ፤ ሚዛኑ ጠፋ ?

ሐምሌ 2007 ዓ ም

ዛሬ፤ ሕዝብን በሀገር ፤ ገበሬን በዕርሻ፤ ስብልን በማሳ፤ እህልን በጎተራ ፤ እንስሳትን በሜዳ፤ ህፃናትን በትምህርት ቤት፤ ቀሳውስትን በቤተ-መቅደስ፤ ሸኹን በመስጊድ፤ ራባዩን በምኩራብ፤ ወታደሩን በጠረፍ፤ ማግኘት ከማይቻልበት ሁኔታ ተደርሷል ። ላወቃቸው፤ ሁሉም የሀገር ቅርሶች ነበሩ። ክብራ ቸውንና ጥቅማቸውን በሚገባ ለተረዳ ዜጋም ፤ ዋጋቸው ከወርቅ፤ ከአልማዝና ዕንቁ፤ ከከበረ ድንጋይም ይበልጥ ነበር ።

በዛሬይቱ ኢትዮጵያ ግን እነኝህ ሁሉ የተከበረ ቦታ አልተሰጣቸውም ። እንዲያውም ቅስማቸው እየተሰበረ እንዲከስሙ እየተደርጉ ናቸው ። ማር ለአህያ እንደማይጥመው ሁሉ ፤ የሀገርን ጥቅም ፤ የሕዝብንም ክብር ፤ የማያውቅ ሥር ዓት አራማጅም እንዲሁ ፤ ለታሪክና ባኅል ዋጋ አይሰጣም ። የራስ ማንነት ገላጮች ስለሆኑ የሀገር ቅርሶች ደንታ አይኖረውም ። ሁሉንም ያጠፉቸዋል። ለታሪክ ቅርስነት እንዳይቆዩ፤ ያፈልሳቸዋል። ለተተኪው ትውልድ ለማስረጃ እንዳያገለግሉ ደብዛቸውን ያጠፉዋል ።

ይህንን የሚያደርገውም፤ ጥንታዊቷና ታሪካዊቷን ኢትዮጵያን አጥፍቶ፤ ቅርሷና መልኳ፤ ማንነቷናም ባልታወቀች ሌላ ሀገር ስም ለመተካት ታስቦ ነው። ነገር ግን፤ ይህ አጥፊ ቡድን ፤ አንድ ያልተገነዘበው ጉዳይ ቢኖር ፤ ወርቁ ቢጠፋም ፤ ሚዛኑ ያልጠፋና የማይጠፋም መሆኑን ነው ። እኛ ደግሞ፤ የተወለድነው፤ ያደግነውና እየታገልን የምንሰዋው፤ ለዚያች ታሪካዊትና ዘለዓለማዊት ለሆነችው ኢትዮጵያ ብቻ ነው። ይህ የጎልውናችን፤ የትግላችንና የመሥዋዕታችን አልፋ-ኦሜጋ ሆኖ፤ በደማችንና አጥንታችን ውስጥ ተዋኅዶ ይኖራል ። እስከ ዘለዓለሙ ! እስከ ምፅዐቱ ! እስኪያልፍ ያለፋል እንጅ፤ መከራው አልፎ ብሩኅ ቀን እንደሚመጣ ግን አንጠራጠርም !

ወያኔን ተፃርረን የምንታገለው መሠረታዊው ምክንያት ይህ ነው ። ይህንን መሰረታዊ ምክንያት አንግበን ለመታገል የማንንም ምክር፤ ፈቃድና ርዳታ አንጠይቅም ። ኢትዮጵያዊነታችን፤ ከምንምና ከማንም በላይ ስለሚበልጥብን፤ በሀገራችን ብሄራዊ ጥቅም ላይ አንደራደርም ። ያንዱ ኃያል መንግሥት መሄድና የሌላው መተካት፤ ይህንን ፅኑ እምነትና አቋም አይለውጠውም ። አንደ በተሃ (?) አፍለኝነት፤ እንደ እስስት ተለዋዋጭነት፤ እንደ እባላ- ባዮች ጥቅመኝነት፤ እንደ ፀሀፍ (?)- ፈሪሳዊ አስመሳይነት፤ ባህርይ የለንም። ለመኖር ብቻ ሲባል ለመኖር የትግላችን መርኅ አይፈቅድልንም ። ይኸው ባህርይና ሰብዕና የመላውን ሕዝብ አመኔታ አትርፎልናል ብለን እናምናለን ።

ምክንያቱም፤ ወርቁ ቢጠፋም ሚዛኑ ስለአልጠፋ ነው ። ሚዛኑ ደግሞ ፤ የኢትዮጵያ ሕዝብ ማለት ነው ። ሚዛንን ከሕዝቡ ጋር ለማዛመድና አንድም ሁሉትም ናቸው ብሎ ለመናገር የሚያስችለው፤ የበለፀገ ታሪክ፤ የዳበረ ባህል ያለው በመሆኑ፤ አባይ ያልሆነ ሚዛን አለው ። ሁሉ-አቀፍ መሥተጋብርና ትክክለኛ የኅሊና ፍርድ ሰጭ ሕዝብ በመሆኑ የማይናጋ ሚዛን ባለቤት ሕዝቡ ነው ። እንደ በተሃ ጥጃ አፍለኛ ያልሆነ ፤ እንደ ብረድስት ሸሮ በቀላሉ የማይገነፍል፤ ለመጣው ሁሉ የማይሰግድ፤ ሥልጣን ለጨበጠ ሁሉ የማያጎበድድና አሜን ብሎ የማይገዛው ፤ በጥቅመኞች ስብከት

የማይታለል ፤ በፍየል ወጠጤዎች ድንፋታ የማይደነብር ፤ በእበላ-ባዮች ወከባ የማይበገር መሆኑን አረጋግጧል ። በዚህ ምክንያት፤ ሚዛኑን አስከብሮ ይኖራል ። ወርቁ ቢጠፋበትም ሚዛኑን አላጣም ። ማንም ሊያሳጣው አልቻለም ። ሕዝቡ፤ ልዕልናውንና ስብዕናውን ከጎሌና ሚዛኑ ጋር አዋኅዶ ቆይቷል። ዛሬም በዚሁ ሁኔታ አለ። ሚዛኑንን ለማንም ሳያስነካ ወደ ፊት መኖሩን ይቀጥላል ። ወርቁን ቢያጣም፤ ሚዛኑን አላጣም ። " <u>ወርቁ ቢጠፉ ሚዛኑ ጠፉ ?</u> የተባለውም እኮ ለዚህ ነበር !

የኢትዮጵያ ሕዝብ፤ የደርግን ጭካኔ ተቋቁሞ የተሻለ አስተዳደር ለማምጣት ሲል ከፍተኛ መሥዋዕት ከፈለ። ግን ፤ ለባሰ አስከፊ ሥርዓት ተጋለጠ እንጅ፤ የከፈለውን መሥዋዕት የሚመጥን ነፃነት እንኳን አላገኘም ። ያም ሆኖ ግን፤ ሚዛኑን ሳያናጋ ክብሩን ጠብቆ ለነገው ብሩኅ ተስፋ ይታገላል ። የሀገር ውስጥ፤ የአካባቢና የዓለም አቀፍ ሁኔታዎች ተባብረው ኅልውናውን ለማጥፋት ቢጥሩም ፤ ሀገራዊና ሕዝባዊ ሚዛኑን ሊያናጉበት አልቻሉም ። ወደፊትም ቢሆን ይደክማሉ አንጅ፤ ኢትዮጵያዊ ሚዛኑን ለማናጋት፤ ችሎታ አይኖራቸውም ። ያም ስለተባለ ኢትዮጵያዊ ሚዛኗን ጠብቃ የምትቀጥለዋን ሀገር አድርጎ ለማቆየት የሚደረገው ጥረት ሁሉ ቀላል ይሆናል ማለት አይቻልም ። ለዚህም በቂ ምክንያቶች አሉ ። የሚከተሉትን እንደ ማስረጃ መጥቀስ ይኖርብናል ።

1ኛ. የሀገሪቱን ችግሮች በሚገባ አለመረዳት ዋነኛው እንደሆነ ይታመናል ።

2. ሀገሪቱ ችግር ያለባት መሆኗ ቢታወቅም፤ እንኳ ፤ ጥልቀቱ፤ ስፋቱና ክብደቱ እስካሁን በቅጡ አልታወቀም ።

3ኛ. ችግሩ በሚገባ ካልታወቀ ደግሞ መፍትሄውን ማግኘት አይቻልም ።

4ኛ. የሀገሪቱ ዋና ችግር ፈጣሪ የሆነው፤ የሀገሪቱ ተወላጅ በመሆኑ፤ የባዕዳንን ሙሉ ትብብርና ድጋፍ ማግኘቱ፤ ችግሩን ውስብስብና ይበልጥ አስቸጋሪ ማድረጉ ። የባዕዳን ወራሪ ኃይል ባለመሆኑ ምክንያት፤ የውጭ ዕርዳታ ለማግኘት ከባድ መሆኑ ።

5ኛ. መፍትሄ ፈላጊ ነኝ የሚለው ክፍል አለመተባበሩ። ይልንቁም፤ ዕርስ በዕርሱ በመከፋፈልና እንዲያውም ለመፍትሄው ፍለጋ ደንቃራ መሆኑ።

6ኛ." የጨነቀው ሙቅ አነቀው " እንዲሉ፤ የሀገሪቱ ዜጎች ራሳቸው መፍትሄ ከመፈለግ ይልቅ፤ ምዕራባውያን መፍትሄ ያማጡልናል ብለው ቀቢፀ -ተስፋን ተስፋ እያደረጉ መጨነቅ፤

7ኛ. የኢትዮጵያን ሕዝብ ዕውነተኛ ማንነት ፤ ባኅርይ፤ ጠባይና ሥነልቦና በሚጋባ ያለመረዳት ችግር፤ እንታገላለን ብለው በሚንቀሳቀሱ ድርጅቶች ወስጥ መኖሩን መካድ አይቻልም ። ለዚህም ይመስላል፤ ብዙዎቹ፤ ኅብረት ፈጠርን ካሉ በኋላ፤ የተፈራረሙበት ሰነድ ላይ ያስቀመጡት ፊርማ ሳይደርቅ ወደ መፈራረስና ወደ ጠብ የሚሄዱት ።

የኢትዮጵያን ሕዝብ በሚገባ ባለማወቃቸው፤ ሕዝብን ወደ ማታለልና እራሳቸውንም ወደ መደለል ተግባር ይሰማራሉ ። ይህ ደግሞ ሕዝቡን በሚገባ ያለማወቅ ችግር ወጤት ነው ። እኛ፤ የኢትዮጵያን ሕዝብ ጠባይና ባኅርይ በሚገባ

እናውቃለን  የሚል ግብዝነት ባይኖረንም ፤  ማወቅ የምንችለውን ያህል ግን በመጠኑም ቢሆን እንረደዋለን  ። ሕዝብን በሚገባ ያለማወቅ  ችግር፤   ከባድ ችግር እንደሆነ   የትግል ተመክሯችን አስተምሮናል  ።

ከብዙ በጥቂቱ፤ እነኝህ ዋና ዋና ምክንያቶች ናቸው ብለን እንገምታለን  ። ችግሮቹ  በቀላሉ  እሳካሁን ሊቀረፈቱ ያልተቻሉት፤ የችግሩ ፈጣሪዎች አምባገነኖች ብቻ ሳይሆኑ፤ እነርሱን ለማሰወገድ የሚችል ኃይል  ለመፍጠር አለመቻላችን ጭምር ሆኖብናል  ።  ይህንንም አውቆ በድፍረት አለመናገር ደግሞ  ራሱን የቻለ  ሌላ ተጨማሪ  ችግር  እየሆነብን ቆይቷል ። እያንዳንዱ  ዜጋ  የራሱን ስኅተት እያወቀ የችግሩ አካል መሆኑን  በድፍረት ካላመነ በስተቀር፤ እናም ለመፍተሄው ፍሊጋ የራሱን  ድርሻ እስካልተወጣ ድረስ፤ የሀገራችንን  ችግር ማንም ባዕድ  መጥቶ ይፈታልናል ብሎ መጠበቅ ግብዝነት ነው። " እራሳችን ያቀለልነውን አሞሌ፤ ሌላ ባለ ዕዳ ሊሸከምልን አይችልም  ። ስህተተን አምኖ መቀበልና  ፈጥኖ  ማረም ፤ ብሎም፤ ይቅርታ መጠየቅ የታላቅነት ምልክት እንጅ፤ የድክመት ነፀብራቅ አይደለም !

የማነኛውም ሀገር መሪ መጀመሪያ ተጠያቂነቱና ኃላፊነቱ ለራሱ ሀገርና ለመረጠው ሕዝብ መሆኑን ሳንገነዘብ ፤ ፐሬዝደንት እከሌ ዋይም ጠቅላይ ምኒስትር እከሌ ሊረዳን ይችላል ብሎ መተማመን፤ የዓለምን  ፖለቲካ ጠባይና አካሄድ አለመረዳት ብቻ ሳይሆን፤ የዋህነትም ጭምር ይሆንብናል  ።  ፐሬዝደንት  ኦፓማ  በቆዳቸው ጠይምነት የተንሳ  ኢትዮጵያን ይረዳሉ ብለው ያመኑ ብዙ የዋሆች እንደነበሩ የቅርብ ትዝታችን ነው፡፡ የሰው ልጅ ለምኞት ባይከለከልም፤  ጠይሙ ፐሬዝዳንት ባራክ ኦባማ፤ የተመረጡት የአማሪካንን ብሄራዊ ጥቅም ለማስጠብቅ መሆኑን ቃለ መሃላ  ወስደው ነው። የአሚሪካ ህግ ተገዥ በመሆናቸውም የሚያገለግሉትም ለአሜሪካ ህግና ደንብ ነው። የአሜሪካ ወታደራዊ- የኢንዱስትሪና ሁል-አቀፍ ጥቅምን ( American- Military - Industrial- Financial  Interest )  ለመጠበቅና ለማስጠበቅ መሆኑን ማጤን ይግባናል ።   እራሱ ያረረበት የሌላውን የሚያማስል ሞኝ  የለም ። ቢፈልጉትም አይገኝም ። እየባከኑ መኖር ብቻ ነው  ትርፉ  ።

የሰሞኑን የኦባማ ኢትዮጵያን መጎብኘት አስመልክቶ  ብዙ  ቲያትሮች ሲውጠነጡኑ ታዝበናል  ።  የእርሳቸው አዲስ አበባ መገኘት፤ የወያኔን ልብና አዕምሮ   ይለውጠው ይመስል፤   እስረኞች ይፈታሉ፤ ወያኔ   የዘጋውን በር ለተቃዋሚዎቹ ይከፍታል  ።  የዴሞክራሲ ጭላንጭል በሀሪቱ  የፖለቲካ መልከዐ- ምድር  ላይ መንዣበብ  ይጀምራል፤  ሥርግና ምላሽ ሆኖ ሕዝቡ በደስታና ሀሴት ይፈነድቃል ወዘተ ተብሏል  ።  የሀገሪቱን የፖለቲካ ሁኔታ በቅርብ የሚከታተሉ  ተንታኞች ያላቸው  ግንዛቤ ግን  ከዚህ ምኞት የተለየ ሆኗል  ። የሚከተሉት ግንዛቤዎች  ያስቀምጣሉ ።

1ኛ.  የኦባማ ጉብኝት የአሜሪካንን ጥቅም በበለጠ ከማስጠበቅ  የተለየ ትኩረት አይኖረውም  ።

2ኛ.  ታማኝ አገልጋይነቱን በተግባር ያስመሰከረላቸውን ወያኔን  አበጀህ በርታ ከማለት ያለፈ ለሕዝቡ የሚጠቅም ፋይዳ አያመጣም ።

3ኛ   የወያኔ አገዛዝ የሚ ጠነከርበትንና በሥልጣኑ ተደላድሎ የሚቀጥልበትን   በበለጠ ከማጠናከር በቀር፤ ለሕዝብ የሚጠቅም ያመጣል ተብሎ አይጥበቅም ። የጠበቀም ካለ እንደናቱ ጡት  ይርሳው።

4ኛ . ኢትዮጵያ፤   የአሜሪካ  ሀረግ ሬሳ  ሪፑብሊክ ( Banana  Republic   ) መሆኗን የሚያረጋግጥ ይሆናል ።

5ኛ. ምናልባት ከእንግዲህ በኋላ፤ ተቃዋሚው ሁሉ፤ አሜሪካ ይረዳናል የሚለውን ተስፋ ሁሉ አሟጥጦ አንድ ላይ ለመተባበር በር ይከፍትለት ይሆናል።\

ይህንን የሚሰማ ሁሉ፤ ( " እባካችሁ አታስጎምጁኝ ") ሊል ይችል ይሆናል፡ ፡

ያም ተባለ ይህ፤ የኢትዮጵያ ሕዝብ ግን ሁሉንም ታዝቦ ጨርሶታል ።

አንቱ ባራክ ኦባማ ያማሪካ ዕንግዳ፤

ጎራ ብለው ነበር በምኒሊክ ግቢ፤ በወያኔ ጓዳ፤

እኛስ መስሎን ነበር እስረኛ ሊያስፈቱ ፤ ከወህኒ ቤቱ ፍዳ።

ለሌላ ጉዳይ ነበር ለካ አመጣጥዎ ፤

ወያኔን መርቀው እኛን መርገምዎ፤

ጨኸታችን ንቀው ጥለው መሄድዎ ፤

መላው የጦቢያ ሕዝብ እንዴት ታዘበዎ ።

ይብላኝ ለርስዎ እንጂ፤ እኛስ አንጎዳም፤ ኢትዮጵያም አትጠፋም፤

ይህንን ለማየት ግን ይቆዩ በሠላም ።

ብሎ ተቸችቶባቸዋል ፤ ለአሚሪካው ፕረዝደንት !

ወትሮውንም ቢሆን በታሪክ፤ ከራሱ በቀር በማንም የማይተማምነው ሕዝብ፤ዛሬ እንደገና ያንን ዕምነቱን በድጋሜ የሚያጠነክርለት ዕድል አግኝቷል ። ሁሉም ነገር ግልፅ ሆኖለታል ። ይኸውም ፤እራሱ ታግሎ ራሱን ነፃ ካላደረገ ፤ ማንም መንግሥት ሆነ ፤ ሀገር ወይም ዓለም አቀፍ ድርጅት ወይም ሰብዓዊና ሃይማኖታዊ ድርጅቶች ነፃ የማያደርጉት መሆኑን እንደገና አረጋግጧል። ሁሉንም አማራጮች ሞክሮ ሞክሮ ስላልተሳካለት፤ አንድ ምርጫ ብቻ ቀርቶታል ። ይኸውም፤ በሁሉም አቀፍ ትግል የታጀበ ሕዝባዊ ኣመፅ! አካሄዶ፤ የራሱ ድል መጎናፀፍ ይሆናል ። ይህ እንዴት ይሳካል ? ማንስ ያሳካዋል ? የሚባሉትን መሪ ጥያቄዎች መመለስ ግን ወሳኝ ነው ።፡

የፖለቲካ ትግል በድል እንዲጠናቀቅ ካስፈለገ፤ የኃይል ሚዛኑን በራስ እጅ ማስገባት አስፈላጊ ይሆናል ። የኃይል ሚዛኑን የሕዝባዊ ወገን ለማደረግ ፤ የፀረ - ሕዝብን አከርካሪ አጥንትና የኃይል ስበት ማዕከል ማስበር የመጀመሪያው ዒላማ ሊሆን ይገባል ። " ዝርዝር ኪስ ይቀዳል " እንዲሉ ፤ ዝርዝር አፈጻጸሙና አካሄዱ በሙያው

የተካኑ ብቁዎች የተግባር ድርሻ ይሆናል ። ይህ በቃል እንደሚያወሩት ቀላል ስላይደለ ፤ ብርቱ ተግባርንና ከባድ መሥዋዕትን መጠየቁ አይቀሬ ነው ። ለዚህ ደግሞ ቁርጠኝነትን ቀጣይነትንና ቆራጥነትን የሚጠይቅ መሆኑን መገንዘብ አስፈላጊ ነው። ይህንን ሳያሟሉ በጥድፊያ የሚደረግ ሽተኪ- በተኪ፤ ሥላማዊውን ሕዝብ አስፈጅቶ - አስጨርሶ " ዘቅዝቆ ሮጠ ወደ ቦንጋ ወንዝ ! " የሚል ትችትንና ፌዝን ከማትረፍ በቀር ፋይዳ አያመጣም ። አስቀድሞ ማሰብ፤ ከታላቅ ጥፋት ያድናል !

ወቅታዊቷ ሀገራችን የሚከተሉትን መልክ ይዛለች ።

1ኛ. የዛሬይቱ ኢትዮጵያ፤ ሁሉ እያላት ሁሉንም እንድትጣ የተደረገች ሀገር ሆናለች ።

2ኛ. ይህ ሁኔታ የ ዓለም ተመፅዋዕች ሀገር አድርጓታል ።

3ኛ. መላው ሕዝቧም ፤ " የመጀመሪያው ምርጫህ ምን እንዲሆን ትፈልጋለህ ? " ተብሎ ቢጠየቅ፤ ያላንዳች ማመንታት ፤ሁሉ፤ ከሀገሩ መውጣትን ያስቀድማል ። ወያኔና ተባባሪዎች ግን፤ ለእነርሱ ብቻ ምድረ-ገነት የሆነችው ሀገር ስለሆነችላቸው ፤ ሌላውን እያባረሩ እነርሱ ይኖሩባታል ።

4ኛ. ዛሬ፤ የሀገሪቱን ስታራተጂያዊ/ ዘላቂ ጥቅም የሚያስጥብቅ ኃይልም ሆነ ማዕከል አለመኖሩ ፤ መፃዒ- ዕድሏ ወዴት አቅጣጫ እንደሚያመራ መተንበይ አልታቻለም ። ሕዝቧ፤ በሜሶፖታሚያ ሀገር፤ በሀረግ ጥንጠልጥሎ እንደነበረ የአትክልት ቦታ እየዋለለ ይገኛል ።

5ኛ. የተቃዋሚው ክፍልም ፤ መልኅቅ ስለሌለው ፤ በከንቱ ይንሳፈፋል ። በመሆኑም የጋራ ስትራተጅ ነድፎ ለመታገል አልቻለም ። ሕዝቡም መሪ አጥቷል ። ተስፋ ቆርጧል ። በተፈራረቁበት ሦስት ሥርዓት ባጋጠመው የጭቆና አገዛዝ ምክንያት ፤ መንግሥት የሚባለውን ተቋምም ሆነ የፖለቲካ ድርጅቶችን ሊያምን አልቻለም ። አይፈረድበት !

6ኛ. የሀገራችንን ያልተነካ ጥሬ ሀብት ለመዘረፍ ባዕዳኑ መልካም አጋጣሚ አግኝተዋል። ያላንዳች ቁጥጥር፤ ይዘርፉታል ። ያሸሹታል።

ኢትዮጵያ ሀገራችን ዛሬ አንድ መሠረታዊ ብቻ ይዛ ቀርታለች። ሚዛኑ ያልተዛባ ጨገሬታዋ ብቻ ! በመሆኑ፤

" ወርቁ ቢጠፋ ሚዛኑ ጠፋ ? " እያለች ለመቆየት ተግድዳለች !

ኢትዮጵያ ለዘለዓለም ትኖራለች !